ከመናገር ማዳመጥ ይሻላል... ይላሉ። ለምን ከተባለ የሚናገር ሰው የሚያውቀውን ነገር ነው የሚደግመው። የሚያዳምጥ ግን ከዚህ በፊት የማያውቀውን ነገር ሊሰማ ይችላል። ከዚያም ነገር ትምህርትና ልምድ ያገኛል። አብደም ይናገር ጤነኛ፣ ልጅም ይሁን አዋቂ፣ የተማረም ይሁን መሃይም እስቲ ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ተናጋሪን ሰው ሳትንቁና ሳታናንቁ አዳምጡ። መደመጥ ያለበት የተማረ ሰው ብቻ ነው ብላችሁ እታስቡ። ሳታስቡ ብዙ ነገር ታተርፋላችሁና ሁሉን አዳምጡ። ያዳመጣችሁትንም እስተንትኑ። ከማስተንተን ብዙ የሚመዘገዘ ነገር ይኖራል።

የሆነ ቀን በአንድ መስጊድ ውስጥ ከዙህር ሶላት በኋላ ደዕዋ ሰማሁና የደዕዋውን ሃሳብና ጭብጥ ለማቆር ብዬ ቶሎ ወጣሁ። ሃሳብ ካላቆሩትና ቶሎ ካልገደቡት ይተንናል። ያላስተዋልኩትና የተለየ እይታ ስለሆነብኝ ላካፍላችሁ ወደድኩኝ -

ኢማሙ እንዲህ ይላሉ፡- "ደጋግ የአላህ ሰዎች ካጋጠሟችሁ ዱዓእ እንዲያደርጉላችሁ አስገድዷቸው።" እንዴት ነው የምናስገድደው ብዬ በማሰብ ላይ እያለሁ እንዲህ በማለት አብራሩልን "ዱዓእ አድርጉልኝ ብትሏቸው ሰዎች ናቸውና ይረሳሉ። ግና እንዲያስታውሱ የሆነ ነገር አድርጉላቸው።" ይላሉ።

ይህ ሲባል ሙስና አሊያም እጅ መንሻ አይደለም። ለምሳሌ አንድ በዲን ጉዳይ ብቻ ለተጠመደ፣ ኪታብ የሚያስቀራ፣ የመስጊድ ጉዳይ ለማስፈጸም የሚሯሯጥ፣ የሙስሊሙን ጉዳይ ጉዳዬ ብሎ ለያዘ... ሷሊሕ የሆነ ሰው የኑሮ ክፍተቱን አይታችሁ በጎ ነገር ብትውሉለት፣ መልካም ነገር ብታደርጉለት፣ የዱንያ ጣጣውን ብታግዙት... በዚያ ባደረጋችሁለት ነገር ሁሌም ያስታውሳችኋል። ይህን ስታደርጉ ለሱ ብቻ እንዳደረጋችሁ ወይም እሱን ብቻ እንደረዳችሁ አታስቡ። ባይሆን ዲኑንም እንደደረዳችሁ ነው የሚታሰበው። እሱ መልካም ነገር በሠራ ቁጥር ምንዳውንም ትጋራላችሁ።

በተለይ አላህ ዱንያን አስፍቶ የሠጣችሁ ሰዎች ይህን ጉዳይ በእጅጉ ብታስቡበት መልካም ነው። ለናንተ ትንሽ መስሎ የሚታያችሁ ነገር ለሌላቸው ህልም መስሎ የሚታያቸው አሉ። ለናንተ ተራ የሆነ ነገር ለነርሱ ቅንጦት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ለናንተ ምንም ያልሆነ ነገር ለሌላው የሰማይ ያህል የራቀ፣ የአለት ያህል የከበደ ሊሆን ይችላል። አንድን ደግ ሰው በእጅጉ ያሳሰበውን ነገር ብታስወግዱለት፣ ፄኦኑን

ብታራግፉለት፣ የቤት ኪራዩን ብትችሉለት፣ ልጁን ብታስተምሩለት፣ ቤተሰቡን ብታሳከሙለት... አላህ ሃሳባችሁን ያራግፍላችኋል፤ ጭንቀታችሁን ያስወግድላችኋል። ደስታውም ሆነ ደስታችሁ ይበዛል። በሙአሚን ልብ ውስጥ ደስታን ማስረጽ ትልቅ ምንዳ አለው። ትልቅ እርካታ አለው።

ለአንድ ዱንያን ችላ ብሎ በዲን ጉዳይ ለተሰማራ ሰው የሆነ ነገሩን ብትጋሩት ሕይወቱ፣ ሕይወታችሁ ይሀናል። ምንዳው ምንዳችሁ ይሆናል። ከዚህም ባለፈ ደግሞ ለምሳሌ, ቤት ብትገዙለት ከፍቶ በገባ ቁጥር ያስታውሳችኋል፣ መኪና ብትሸልሙት ድካሙ ቀልሎ በታየው ቁጥር ይመርቃችኋሃል፣ ልብስ ገዝተህ ብትሠጠው በለበሰው ቁጥር በዱዓእ ያስብሃል፣ ጠቃሚ መጽሐፍ፣ ኮምፒዩተር፣ ሞባይል አሊያም ሌላ ነገር በስጦታ ብትሠጠው... ባነሳው ቁጥር ያወሳሃል። መልካም በሠራበት ቁጥርም አንተም የምንዳው ተካፋይ ትሆናለህ።

በመጨረሻም ዳዒው ይህችን ቀልድ ነገሩንና ደዕዋቸውን አሳረጉ። የሆነ ዘራፊ ከአንድ ሸህ ልብሳቸውን ገፈፈና ራቁታቸውን አስቀራቸው አሉ። ይባስ ብሎ ደግሞ "ሸሃችን ሆይ በዱዓ እንዳይረሱኝ።" አላቸው አሉ። ሸሆቹም "ለነገሩ ብርዱስ ቢሆን መቼ ያስረሳኝና" አሉት አሉ።

ገብቷችኋል አይደል... ነገሩ እንደዚያ ነው። የአላህ ደጋግ ሰዎችን ተወዳጁ። ለአላህ ብላችሁም ውደዷቸው። እንደነርሱ በዲን ጉዳይ ‹መሸጉል› ባትሆኑ ለነርሱ የሚያስፈልገውን ነገር አሟሉላቸው። በዚህም እንዳይረሱ አድርጋችሁ ዱዓእ አድርጉልን በሏቸው። አላህ ዘንድ ሰውም ከሰው ይሻላል። የሰው ልጅ የመደመጥ ኃይሉ እንደ ደግነቱና ንጽሕናው ነው። መልካምና መጥፎ ሰው እኩል አይደለም። ከፊት ያለና ኋላ የቀረ እኩል አይደለም።

ሰው ለእኩይ ዘመቻው፣ ለውሸትና ለጥላቻ ሃሳቡ... ቴሌቭዥን ልከፍት ነው፣ ተቋም ልመሠርት ነው ብሎ እንኳ ይለምን የለ! ያለ እፍረትና ኃፍረት እርዱኝ ይል የለ!። መልካምና ደጋግ አስተማሪ ሰዎችን እባካችሁ እርዷቸው። መልካም አስበው እጃቸው ያጠረ ሰዎች፣ በሙሉ ኃይላቸው ለዲኑ ይሠሩ ዘንድ፣ ትኩረታቸውን የሚሠርቅ የዱንያ ሃሳብ እንዳይኖር የችግር ቀዳዳቸውን ድፈኑላቸው።

በደጋጎች ዘመን እነ ዐብዱላህ ኢብኑ ሙባረክ የዲን ሰዎችን "እናንተ ዲንን አስተምሩ፤ የእናንተን የኑሮ ጣጣ መቻል የኛ ጉዳይ ነው" ይሉ ነበር። በአገራችንም ዲን

የተስፋፋበት አንዱ መንገድ የዲን ሰዎችን ዱንያዊ ጣጣ በመቻል ነው። ስፖንሰርነት ማለት ይኸው ነው። ነጋዴዎቻችን በገንዘባችሁ ፎቅ ለመሥራት ብቻ አትቀሽዳደሙ፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዲንን በማጣዘ፣ በማስተዋወቅና በመከላከል ላይ የተሠማሩ ወጣቶችንም እርዱበት።

ብልህ ሰው በገንዘቡ መልካም ነገር ያሠራል፣ ዱዓእ ያስደርጋል፣ ጀነትንም ይገዛል።

ደስም ይልሻል!

ይህችን እውነተኛ ታሪክ ጣል ለማድረግ አሰብኩ ...

ዲኔ ላይ ደህና ነኝ። መልከ አለኝ ባይባልም አልከፋም። በባህሪዬ ደህና ነኝ ብዬ አስባለሁ። ከቤተሰብ ሳልርቅ ነው ያደግኩት። የልጅነት ጊዜዬ አልፎ ወጣትነት መጣ። እንደማንኛዋም ሴት ትዳር አሰብኩ። ግና በማላውቀው ምክንያት ዘገየብኝ። በሚገርም ሁኔታ ለጋብቻ የሚጠይቀኝ ጠፋ። ከኔ በኋላ የተወለዱ የቤተሰብም፣ የዘመድም፣ የሰፈርም ልጆች አንድ በአንድ አገቡ። ተራ በተራም ወለዱ። ልጆቻቸውም አደጉ። ሳላስበው 34 ዓመት ሆነኝ። ዕድሜዬን ሳስታውሰው ደነገጥኩ። ብቻዬን ቆሜ የቀረሁ እስኪመስለኝ ድረስ ተሠማኝ።

የሆነ ጊዜ ከቅርብ ዘመድ የሆነ አንድ ወጣት ለጋብቻ ጠየቀኝ። ፈቃደኝነቴን ገለጽኩለት። ሁለት ዓመት ይበልጠኛል። ዲኑም ፀባዩም ቆንጆ ነው። ደስ አለኝ። ከሃሳቤ የተገላገልኩ መሰለኝ። ቤተሰብም ደስ አለው።

ኒካሕ ለማሰር ተዘጋጀን። አንዳንድ ጉዳዮችን ለመጨረስ ብሎ መታወቂያዬን ይዞ ሄደ። ከሁለት ቀን በኋላ ስልክ ተደወለልኝ። እናቱ ነበረች። እንደምትፈልገኝ ነገረችኝ። ምን ይሆን ብዬ እየበረርኩ ሄደኩኝ። ቤታቸው ገባሁ። ጥቂት ካወራን በኋላ መታወቂያዬን እያሳየችኝ እዚህ ላይ የተጠቀሰው የትውልድ ቀኔ ትክክል ስለመሆኑ ጠየቀችኝ። "እውን ትክክል ነው" አልኳት።

"እንግዲያውስ አንች አርባ ተጠግተሸል መውለድ አትችይም!" አለችኝ።

"ገና 34 ዓመቴ እኮ ነው! እንዴ አንዴት አልችልም?" አልኳት።

"አይ... አንች ሰላሳ አልፎሻል፤ እኔ ደግሞ ልጅ አይደለም፣ ገና የልጅ ልጅ ማየት አፈልጋለሁ።" አለች።

ጋብቻው እንዲሰረዝ ሞገተች። ልጇንም አሳመነች። ጋብቻው ተሰረዘ። ለቤተሰቤ ምን እንደምላቸው እያሰላሰልኩ ተስፋ ቆርጬ በሐዘን ተውጬ ወደቤቴ ተመለስኩ።

ቀናት አለፉ። ድፍን ስድስት ወራትን በሐዘን አሳለፍኩ። ረጃጅም ቀንና ሌሊቶችን ስብሰለሰል ከረምኩ። በር በሩን ባይ እኔን ብሎ የሚመጣ ለኔ የተፃፈ ባል ጠፋ። ብቸኝነት፣ ባይተዋርነት፣ አጥንት ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ።

አባቴ ሁኔታዬን ይከታተላል። ስለኔ አብዝቶ ተጨነቀ። በመጨረሻም ከወንድሜ ጋር ለዑምራ እንድሄድ መከረኝ። "ሂጂና በተከበረው የአላህ ቤት አጠገብ ብሶትሽን ተናገሪ፤ የውስጥሽን የውስጥ አዋቂ ለሆነ ጌታ ተንፍሺ" አለኝ።

ሄድኩኝ። የአላህ ቤት ከዕባ ፊት ቁጭ ብዬ ረጅም ዱዓ አደረግኩ። ለርሱ የውስጥ ስሜቴን ሁሉ አንሾካሽኩ። አለቀስኩ፤ እፎይታዬን ያቀርብልኝ ዘንድ ተማፀንኩት።

የሆነ ቀን ሱንና ከሰገድኩ በኋላ ጥቂት ቁጭ አልኩ። ከኋላዬ አንዲት ሴት ባማረ ድምጽ ቁርአንን ታነባለች።

"የአላህ ችሮታ ብዙ ነው።" የሚል ትርጉም ያለውን የቁርአን አንቀጽ ስታነብ ቀልቤ በተለየ መልኩ ወደዚያ ተሳበ። በቁርአን ውስጥ የዚህ ዓይነት አንቀጽ ስለመኖሩ ገረመኝ። አላህ በችሮታው ያስበኝ ዘንድ ተማፀንኩት።

ሴትዮዋ አየችኝ። ምን እንደሆንኩ ጠየቀችኝ። ሁኔታዬን ነገርኳት። "አብሽሪ" አለችኝ "አብሽሪ አላህ ያሰብሽውን ይሠጥሻል፤ ኢንሻአላህ ደስም ይልሻል።" አለችኝ።

ዑምራውን አጠናቅቄ ተመለስኩ። ድንገት የረጅም ጊዜ ጓደኛዬንና ባሏን በአይሮፕላን ማረፊያው አገኘኋቸው። የባሏን ጓደኛ ለመቀበል እየጠበቁ ነበር። ሰላምታ አቅርቤላቸው ትንሽ አንዳወጋን ጓደኛቸው ደረሰና ተሰነባበትን። ወዲያው አባቴ ደርሶ ተቀበለኝ።

ጥቂት ቀናት አለፉ። አሁን ከበፊቱ በተሻለ ልቤ በመጠኑ ሰከኗል። ዱዓዬን አላቋረጥኩም። የሆነ ቀን ያች አይሮፕላን ጣቢያ ያገኘኋት ጓደኛዬ ደወለችልኝ። ያን ቀን ያየኝ የባሏ ጓደኛ ለትዳር እንዳሰበኝ ነገረችኝ። በአንድ ቀን እይታ እንዴት ሊሆን ይችላል? ብዬ ተገረምኩ። ግና ለአላህ ምን ይሳነዋል!!።

በእውነቱ የማይታሰብ ነገር ሆነብኝ፤ ማመን አቃተኝ። እሱ ግን የምሩን ነበር። ስለኔ ሁሉን ነገር ከጓደኛዬ ከሰማ በኋላ አላንገራገረም። ወደ ቤተሰቦቼ ሽማግሌ ላከ። ደስ አለኝ። ተስፋዬ ለመለመ። ወዜ ተመለሰ። ስሜቴ ታደሰ።

አገባሁ። ጥሩ አፍቃሪ፣ መልካምና ደጋፊ፣ አዛኝና አሳቢ ባል... አላህ ሠጠኝ። ለኔም ለወላጆቹም ጥሩ ሰው ነበር።

ካገባሁ ቀናት ሄዱ፣ ሁለትና ሦስት ወራት ተተኩ። ሌላ ሃሳብ አስጨነቀኝ። የእርግዝና ምልክት ናፈቀኝ። ግና እስካሁን በራሴ ላይ ምንም አላስተዋልኩም። ሲበዛ አሳሰበኝ። እንቅልፍ አጣሁ።

መመርመር እንደምፈልግ ለባሌ ነገርኩት። ወደ ሐኪም ቤት ሄድን። ጥቂት ቆይተን ለውጤቱ ተጠራን። ልቤ መምታቱን ጨመረ። ግና እንደገባሁ "ማዳም መብሩክ!" አለችኝ ሐኪሚ።

እርግዜ ነበር። ሱብሐነላህ!። 'ለዚህ ብስራት ነበር እንዴ አላህ አዚህ ድረስ ያመጣኝ!' አልኩ። የእርግዝና ጊዜዬ ሰላማዊ ነበር። ግና የዕድሜዬ መግፋት መጠነኛ ተጽእኖ ነበረው። ሆዴ እያደገ ሲመጣ ሰውነቴ ከበደኝ። እንደምንም የድካሙ ወራት አለፈ። የምጡ ቀን ደረሰ። በቀዶ ጥገና ነበር የወለድኩት። ከተሠጠኝ ሰመመን ሰነቃ ቤተሰቦቼና ባለቤቴ ዙርያዬ ተሰብስበዋል። ይስቃሉ፣ ይጫወታሉ።

"ምን ወለድኩ?" አልኳቸው ያለሁበትን ሁኔታ እያስታወስኩ።

የተመካከሩ ነበር የሚመስለው። አንድ ላይ ሆነው ነበር ሰርፕራይዝ ያደረጉኝ "ወንድ እና ሴት!" አሉኝ። መንታ!!። የኔን መንቃት ሲጠብቅ የነበረው ባሌ በደስታ ተፍነከነከ። እኔንም ሀሴት የምሆነውን አሳጣኝ። ብችል ተነስቼ በዘለልኩ። ቁስሌ ገና እርጥብ ነው። ሱጁድም ራቀኝ። በተኛሁበት እንባዬ በሁለቱም ጉንጮቼ በኩል ዝምብሎ ሲፈስ ይታወቀኛል። በትኩስ እንባ ፊቴ ታጠበ። ምስጋናዬን ያወጣሁበት ቃል እሱ ነበር።

ያቺ "አላህ ያሰብሽውን ይሠጥሻል፤ ኢንሻአላህ ደስም ይልሻል!።" ያለችኝ ሴት ትዝ አለችኝ። የቂን ይሏል ይህ ነው!!

‹ወለሰውፈ ዩዕጢከ ረቡከ ፈተርደ› የሚለውን የቁርኣን አንቀጽ አስታወስኩ። ስለ አላህ አሰብኩና በሃሳብ ርቄ ሄድኩ። የሱ ሥራ አብዝቶ ገረመኝ። እኛ ተስፋ እንቆርጣለን እንጂ፣ እሱ ያዘጋጀልን ነገር አለ። እኛው ሁለት ልብ ሆነን ተቸገርን እንጂ፣ በርግጠኝነት በአንድ ሆነን ልብ ይሠጠናል ብለን ብንለምነው ይሠጠናል። እኛ ከሱ ራቅን እንጂ እሱ ሁሌም ከኛ ጋር ነው። እኛው እንቸኩላለን እንጂ፣ እሱ ለሁሉም ነገር መላና መፍትሄ አለው፤ ለሁሉም ነገር ምክንያትና ጊዜ አለው። ለአላህ ውሳኔ መታገስና ፈረጃውን መጠበቅ ትልቅ ዒባዳ ነው።

እንኳን እኛ ነቢዩ ዘከርያም በልጅ እጦት ተፈትነዋል። "ጌታዬ ሆይ ብቻዬን አትተወኝ..." ሲሉ ነበር ዱዓአ ያደረጉት።

በልጅ ናፍቆት የተሰቃየሽ አህቴ ሆይ! ኢንሻአላህ ፈጣሪሽ ያሰብሽውን ይሠጥሻል፤ እንቺም አንድ ቀን ደስ ይልሻል!።

"ቂሰሱን ሚነል ዋቂዕ" ከተሠኘ መጽሐፍ የተወሰደ።

ሙሐመድ ሰዒድ (ABX) አንደተረጎመው

ተስፋ የቆረጡ ሁሉ ተስፋቸው ይለመልም ዘንድ አንብቡላቸው።